# በርበሬ አጥኖ መስቀል

ከወያኔ በላይ ፣ ወይኖ አዳሪ
ባገር የተተፋ ፣ የተናቀ አዝማሪ
እዩኝ እዩን ይላል ፣ ቋምጦ ፍርፋሪ
ኳኩሎ አሳመረው ፣ አረኸጡን ፈሪ
ለንቃው እስኪላቀቅ ፣ ይልብናል አሪ ።

ዘመን በሸቀጠ ፣ አግዜሩም ተቆጣ
ቀጥተኛ ጠፍቶ ፣ ሰልጥኖ ጎባጣ
መጣ ባገራችን ፣ ያዝማሪ ቀልብ ያጣ
ቅንድብ ፣ ቅንድብ የሚል ፣ የሚሞገስ ቢያጣ
ያውም የደደቢት ፣ የበረሃን ፈንጣ ።

ከተሞገሰ አይቀር ፣ ሌላው ለምን ቀረ
የደሃ አጥር መስሎ ፣ የተውገረገረ
በቢጫ ቀለማት ፣ የተሸቀረቀረ
ከንፈሩን ተሻግሮ ፣ አውጪ ያደረ
ሰለ ጥርሱስ ውበት ፣ መቼ ተዘከረ ።?

አፍንጫውስ ቢሆን ፣ ምን ይወጣለታል
ዝንጅብል መስሎ ፣ መልኩን አስውቦታል
ለአበባ ባይሆንም ፣ ጥንብ ያሸትለታል ።

ጸጉሩ ወርዶ ወርዶ ፣ ቢወድቅም ተንዶ
ባዶ ቅል ቢያደርገው ፣ እንደ ህሊናው ባዶ
በመሀል አናቱ ፣ ቦይ ሰርቶ ተቀዶ
ለጥፋት ለውድመት ፣ ለክፋት ተጠምዶ
ቁርና ሀሩሩን ፤ ይኖራል ተላምዶ ።

ምነው አይዘፈን ፤ ሸበላ ተብሎ
ኩርኩር ቢሆንም ፤ እዚያው ተድበልብሎ
በለመደ ምላስ ፤ የሌለን ቀጥሎ
ሰው ከሩቅ እንዲያየው ፣ ባቀንቃኙ ታዝሎ ።

ዝንብ ንብ ነኝ ብላ ፣ ካወራች ጀምሮ
ምን ያልተባለ አለ ፣ ጉድ ያሰማል ጆሮ ።
ላዝማሪ ቀልማዳ ፣ ለአጋሰስ ወደል
አስር ቦታ ረጋጭ ፣ ለሚወድ መፈደል
ቅንድባም ወያኔ ፤ አገርን ለሚያቀል
ቁልቁል ሁለቱንም ፣ በርበሬ አጥኖ መስቀል ።

ታዛቢው … May 26, 2010